የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ግንቦት 19 /2003

# ለተግባራዊ ትብብር ሌላ አማራጭ የለውም

ህብረት ሲሉ ህብረት ስንል በሚል በተደጋጋሚ የኢሕአፓን አቅዋም ያቀረብን ሲሆን በአሁ
ኑ ጊዜ በየአቅጣጫው ህብረት ምስረታ በሚል ብዙ እየተደመጠ በመሆኑ ኢሕአፓ እንደገና
አቅዋሙን ግልፅ አድርጎ ማቅረብ ይገደዳል።

በደፈናው ህብረት፥ ህብረት ማለቱ ፋይዳ ቢስ መሆኑን በተመክሮ የተገነዘብነው ነው።
ህብረት ከማን ጋር የሚለውን ጥያቄ መመለስ የምንችለውም ህብረቱ ለምን ግብ ነው
የሚለውን በሚገባ ስንረዳ ነው። ለመለስተኛ ዓላማ መተባበር ቢቻልም መሠረታዊው ህብረ
ትግን፥ከዚህ በፊት በወጣ መግለጫ እንዳሰፈርነው፥ ሕዝብን ለአመፅ ለማደራጀትና፥ ለማነ
ሳሳትና የወያኔንም አገዛዝ ለመጣል ነው። ህብረት የሥርዓት ለውጥን ለማምጣትና ዴሞክራ
ሲን ለማስፈን መሆን አለበት። በመሆኑም ህብረት ከማን ጋር ስንልም በሀገር ቤት ህልውና
ካላቸው ድርጅቶች ጋር፤ የወያኔን አገዛዝ በማስወገድ ከሚያምኑት ጋርና በኢትዮጵያ
አንድነት ላይ የማያወላውል አቅዋም ካላቸው ጋር መሆን አለበት ሲል ኢሕአፓ ማመኑንም
ገልፆ ነበር ። ከዚህምመደምደሚያ የደረሰው በበርካታ ህብረት ጥረቶች ተካፍሎና አዎንታ
ዊና አሉታዊ ተመክሮንም ቀስሞና ገምግሞ ነው።

ለዚህም ነው በዚህም በዚያም -- አንዳንዴም ከቶ ይህ ነው የሚባል ህልውና በሌላቸው --
በሚጠራ የህብረት ጥረት ውስጥ አልሳተፍም ያለውና እያለም ያለው። ትብብርና ህብረት
ከተፈለገ በተግባር፤ በሀገር ፤ በትግሉ መድረክ ተገናኝተን እንተባበር ብሎ ጥሪ ያቀረበው
ለዚህም ነው። ዛሬም ቢሆን ስለ ህብረት እየተወራ በተጨባጭ በሀገር ትግል ህብረትና
ትብብር ያልሰፈነበት ሁኔታ እንዳለ የምናየው ነው። ለተግባራዊ ትብብር ማለትም በሀገር
ቤት በትግሉ መስክ ለሚደረግ ወይም መደረግ ለሚገባው ትብብር ሌላ አማራጭ የለውም።
ስለዚህም ኢሕአፓ ህልውና ላላቸውና በኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት ለሚያምኑ ድርጅ
ቶች፤በተጨባጭ ፀረ-ወያኔ ትግሉን በሀገር ቤት ውስጥ ትብብርና ህብረትን እንሻ፤ እንሞክር
ሲል ጥሪውን ያቀርባል።

**EPRP**
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

**EPRP**
BP 22
Bois Colombes 92270
France

**E-mail** ESPIC@aol.com **Website:** http://www.EPRP.com